ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

**Draft… not for press release -**

Date - Sep. 7, 2006
No. KIL_PR_AMH006

# በደረሰው አደጋ አዝነናል… በአቶ አዲሱ ለገሰ አፍረናል!!

በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በደረሰው የተፈጥሮ አደጋ ልባችን በሃዘን ተመትቷል። ከዚህ ቀደም በልዩ ልዩ ሚዲያዎች በገለጽነው መሰረት፤ በድሬደዋና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች፤ በህዝባችን ላይ የደረሰው አደጋ አሳዛኝ ነበር። የዚህ አደጋ መድረስ እንደተሰማ በትንሳዔ ሬዲዮ አማካኝነት ጉዳት ስለደረሰባችው ቤተሰቦች ያለንን ጥልቅ ስሜት አሳውቀናል።

ዛሬ በድጋሚ ለህዝባችን የምንለው ነገር ቢኖር፤ "በሰሜን፣ በደቡብ፤ በምስራቅና በምዕራብ ክልሎች በደረሰው የተፈጥሮ አደጋ ሃብት ንብረታችሁን ያጣችሁ፤ ወዳጅና ቤተሰብ የተለያችሁ በሙሉ አምላክ ፅናቱን ይስጣችሁ። መጪውም ዘመን የሰላምና የፍቅር ይሁንላችሁ" እንላለን። የተፈጥሮ አደጋው በደረሰ ጊዜ ዘርና ሃይማኖት ሳትለዩ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ፤ የችግርን ዘመን በማሳለፋችሁ ኮርተንባችኋል። እውነተኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋነትና አንድነት ጠብቃችኋልና በመጪውም አመት አንድነታችሁን ጠብቃችሁ፤ ከዚህ ለተሻለ ድል እንደምትበቁ ተስፋችን ፅኑ ነው።

የአገራችን ህዝብ እንዲህ በአንድነት ለህዝብና ለሃገሩ በቆመበት ወቅት፤ የወያኔ ኢህአዴግ ሹመኛ፤ የመለስ ዜናዊ ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር የሆኑት አቶ አዲሱ ለገሰና የአማራው ክልል ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ አያሌው ጎበዜ፤ የዘር ልክፍት አባዜ ይዟቸው በአሜሪካ ክፍለ ግዛቶች ጉብኝት ማድረግ ጀምረው ነበር። በተለይም አቶ አዲሱ ለገሰ በአሁኑ ወቅት በጎርፍ ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖቻችን ለመርዳት በተቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ በዋና ሊቀ መንበርነት ቢመረጡም፤ ይህንን ታላቅ ወገንን የማዳን ተግባር ወደ ጎን በመተው ግብረ አበራቸውን አስከትለው የአሜሪካ ጉብኝት ቀጥለው ነበር… የከረሙት።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ህዝብ በጎርፉ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን፤ በዘርና በሃይማኖት ሳይለይ እየሰጠ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ አቶ አዲሱ ለገሰ በአሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በዘር ለመከፋፈል ካላቸው ፍላጎት በመነሳት፤ የአማራ ብሄር ተወላጆችን ነበር… ስብሰባ የጠሩት።

በአሜሪካ ክፍለ ግዛቶች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ግን ለአቶ አዲሱ ለገሰ መሰሪ ተግባር አልተገዙም። ይልቁንም አቶ አዲሱ ለገሰ በየደረሱበት ሁሉ፤ የገደሏቸውና ያስገደሏቸው ደም ሲጮህባቸው ነበር። በየሄዱበትም ቦታ ሁሉ… ያሰሯቸውንና ያሳሰሯቸውን እንዲፈቱ ተጠይቀዋል። በአሜሪካ ክፍለ ግዛት በሚገኙት፤ የሳን ሆዜ፣ የሲያትል፣ የቦስተን፣ የአትላንታ፣ የኦሃዮ እና የዋሺንግተን ዲሲ ከተሞች አቶ አዲሱ ለገሰ ተዋርደውና አፍረው ተመልሰዋል። ይህ እፍረትና ውርደት ደግሞ ለአቶ አዲሱ ለገሰ ብቻ ሳይሆን፤ ለሚወክሉት የወያኔ/ኢህአዴግ ድርጅት የሞት ጥሪ ደወል ነው።

በአገራችን ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችን በደረሰባቸው የተፈጥሮ አደጋ ልባችን ክፉኛ አዝኗል። እነዚህን ወገኖቻችንን ለመርዳት ዘርና ወገን ሳይለዩ ታላቅ ተግባር የፈጸሙ ኢትዮጵያዊያን አኩርተውናል። የተቋቋመው ኮሚቴ ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ አዲሱ ለገሰ ግን ተግባራቸውን ስተውና ረስተው በአሜሪካ ከተሞች ሲንፈላሰሱ ማየት፤ በቁጭት አብከንክኖናል። በጎርፍ አደጋ የተጎዱት ወገኖቻችን የሚያድሩበት ድንኳንና የሚበሉት ጥሬ ባጡበት ባሁኑ ወቅት፤ ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር የተባሉት አቶ አዲሱ ለገሰና የአማራው ክልል ሊቀ መንበር አቶ አያሌው ጎበዜ በአሜሪካ ሊያደርጉ አስበው የከሸባቸው ስብሰባ፤ ለሃላፊነት ብቁ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ጉልህ መነጽር ነበር።

በአጠቃላይ ዘርና ሃይማኖት ሳትለዩ ለተጎዱት ወገኖቻችን ለደረሳችሁ በሙሉ… በሳን ሆዜ፣ በሲያትል፣ በቦስተን፣ በአትላንታ፣ በኦሃዮና በዋሺንግተን ዲሲ አቶ አዲሱ ለገሰን አሳፍራችሁ ለሸኛችሁት ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

መልካም አዲስ አመት

የቅንጅት አለም አቀፍ የህዝብ ግንኙነት ክፍል።